# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

**ስብሰባ ከኳየርና ከአምልኮ ቡድን አባላት ጋር**

ዛሬ ከአምልኮ ጊዜ በኋላ ከኳየርና አምልኮ ቡድን ጋር ስብሰባ ስለሚኖረን በዚህ አገልግሎት ያላችሁ ሁሉ በሰብሰባው ላይ እንድትገኙ ሽማግሌዎች በማክበር ይጠይቃሉ።

**የእሁድ 1:30 ጸሎት**

እሁድ ልክ 1:30 ላይ ተገናኝተን በጸሎት እንድንተጋ ቤተ ክትርስትያን አጥብቃ ታሳስባለች። በተከታታይ በዚህ ሰአት በእግዚአብሔር ፊት የምንጸልይባቸው ጉዳዮች ስላሉን ልክ በሰዓቱ እንድንገኝ እናሳስባለን።

**የአርብ ፕሮግራም**

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በተለይም ደግሞ አሁን እስከ አመቱ መጨረሻ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ እንጸልያለን። አመቱን እንዋጃለን። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

# የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።" (ማቴ. 16:18)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.

**January 13, 2019**

**ታህሳስ 28፣ 2011 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

ጸሎት መሪ................. ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ

አምልኮ....................... የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን

ፕሮግራም መሪ .......... ወ/ም ጸደቀ ጴጥሮስ

ቃል ............. ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ

ማጠቃለያ ................. ፕሮግራም መሪ

**<u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>**

"እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥
ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ።
ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም
ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥
ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤
ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና።"
(ማቴ. 11:28-301)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| **መሪ** | **ቀን** | **አድራሻ** |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ምስክሮች

በፈለገ-አብርሃም ለጥሪው ልታዘዝ፣
በስራ ሚገለጥ የምነትን ፅድቅ ልያዝ፣
በመንፈሱ እንዳየ ከሞተ ኣካል ህይወት፣
ያስነሳዋል እንዲል ልጅ አቅርቦ መስዋኢት፣
እኔም ድልን ላብስር ትንሳኤውን ላሽትት።

የልብ ብርህን ስጠኝ እንደ ባርያህ ሙሴ፣
ከግብፅ ተድላ ይልቅ እንድትሻህ ነፍሴ፣
ያለም ዝና ሚያስንቅ ክብርህን አይቼ፣
ጉልበቴ ሳይደክም ሳይፈዙ አይኖቼ፣
በከፍታ ልሙት ተራራ ወጥቼ።

እግሬ ዘይት ይጥለቅ በአሴር ምሳሌ፣
እድሜዬም ሲጨምር እንዲታደስ ሃይሌ፣
ይሞላ ጎዳዬ በሚተርፍ በረከት፣
ቀባኝ በመንፈስህ አጫማኝ በብረት፣
ጠላቶቼን ላድቅቅ በስምህ ሃይል ጉልበት።

ታምነው እንደሄዱት ካሌብና ኢያሱ፣
ባንተ አይን ልያቸው ጥላቶቼ ይነሱ፣
እንደ ተናገረኝ እንደሁ ይሆናል፣
ብዬ ልሰማራ አንግቤ የተስፋ ቃል፣
ተራራውን ልውረስ አስለቅቄ በኃይል።

ባንተ ደስ ይበለኝ እንደ ልብህ ዳዊት፣
ሳልቆጥብ ላምልክህ በፊትህ ልጫወት፣
በስምህ ወንጭፌ ጎልያድን ልጣል ላስወግድ
ተግዳሮት፣
በትውልዱ መሃል እዳገለገለህ በሃሳብህ ቅኝት፣
ለኔም ክብሬ ይሁን በዘመኔ መሮጥ መፈለግ ያንተን
ፊት።

ለጳውሎስ ያበራው የክብርህ ብርሃን፣
አብዝቶ ይክፈተው የኔንም የውስጥ አይን፣
ምልክትን ልፍጠን ልዘርጋ ወደ ፊት፣
ተጋድሎዬ ይላቅ በሚጨምር ቅባት፣
የማዳኑን ወንጌል ላብስር ለፍጥረታት።

እኔም እንደ ማርያም እንደ መቅደላዊት፣
በእግሮችህ ስር ልረፍ ልቀመጥ ለመስማት፣
እግርህ ላይ ላፍስሰው ሽቶዬን ሰብሬ፣
በፀጉሬም ላብሰው ትስገድልህ ክብሬ፣
ባንተ ምህረት ነው በህይወት መኖሬ።

ጥቂት እናንሳ እንጂ እንዲሆኑን አብነት፣
የኃይሉን ብርታት የቀመሱ ድል የነሱ በእምነት፣
ደግሞም የሚበልጠውን ክብር አይተው፣
አምነው የሞቱ ስለ እምነትም የተሰው፣
እንደ ደመና የከበቡን የሚያበረታን ፈለጋቸው፣
ቀድመውን የጨረሱ ምስክሮቹ ብዙ ናቸው።

ደግሞ አለ በፊቱ ስላለው ደስታ ነውርን ንቆ
በመስቀል የታገሰ፣
አዲስ መንገድ ጠርጎ በፊታችን የሄደ ሩጫውን
የጨረሰ፣
ምት ሊይዘው ያልቻለ አሸንፎ በህይወት የነገሰ፣
የድላችን ብስራት የእምነታችን እራስ፣
ሊቀ ካህናችን ቀዳሚው ኢየሱስ።

የምስክሮቹን ፋና ተከትለን ይልቁንም እያየን
ጌታችንን፣
ቶሎም የሚከበንን ሃጥያት አስወግደን ሸክምን ሁሉ
ጥለን፣
ከዝለትና ከእንቅልፍ ከመታከትም ወጥተን፣
ቀንዲላችንን ዘይት ምልተን ኃይላችንም እንደ ንስር
አድሰን፣
በተጨመረልን እድሜ በተሰጠን አዲስ አመት፣
እንገስግስ ወደፊት ሩጫችንን እንሩጥ በትግስት።

(ረድኤቱ Dec. 2018)